የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳
አዲስ አበባ ጥር ፲፱ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 20
ADDIS ABABA 27th January, 2009

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፳/፪ሺ፩ ዓ.ም

በመርከብ የፍጆታ ነዳጅ ፍሳሽ ሳቢያ ለሚደርስ የከባቢ ብከላ ጉዳት ስለሚኖር የፍታብሔር ኃላፊነት አስመልክቶ የወጣውን ኮንቬንሽን ማጽደቂያ አዋጅ… ገጽ ፬ሺ፬፻፵፰

CONTENTS

**Proclamation No. 620/2009**

The Civil Liability for Bunker Oil Pollution Damage Convention Ratification Proclamation …..Page 4448

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፳/፪ሺ፩

## <u>በመርከብ የፍጆታ ነዳጅ ፍሳሽ ሳቢያ ለሚደርስ የከባቢ ብከላ ጉዳት ስለሚኖር የፍታብሔር ኃላፊነት አስመልክቶ የተደረገውን አለም አቀፍ ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>

እ.ኤ.አ. በ፪ሺ፩ አለም አቀፉ የማሪታይም ድርጅት በመርከብ የፍጆታ ነዳጅ ፍሳሽ ሳቢያ ለሚደርስ የከባቢ ብከላ ጉዳት ስለሚኖር የፍትሐብሔር ሃላፊነት አስመልክቶ አለም አቀፍ ኮንቬንሽን ያወጣ በመሆኑ፣

ይህንኑ ኮንቬንሽን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክ ራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሣሥ ፳፫ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "በመርከብ የፍጆታ ነዳጅ ፍሳሽ ሳቢያ ለሚደርስ የከባቢ ብከላ ጉዳት ስለሚኖር የፍታብሔር ኃላፊነት አስመልክቶ የወጣውን ኮንቬንሽን ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፳/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 620/2009.

## <u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE INTERNATIONAL CONVENTION ON CIVIL LIABILITY FOR BUNKER OIL POLLUTION DAMAGE</u>

**WHEREAS,** an International Convention on Civil Liability for Bunker Oil Pollution Damage has been adopted by the International Maritime Organization in 2001;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Convention at its session held on the 1st day of January, 2009;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

### 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as "The Civil Liability for Bunker Oil Pollution Damage Convention Ratification Proclamation No. 620/2009".

## ፪. የኮንቬንሽኑ መጽደቅ

በመርከብ የፍጆታ ነዳጅ ፍሳሽ ሳቢያ ለሚደርስ የከባቢ ብክላ ጉዳት ስለሚኖር የፍታብሔር ኃላፊነት የአለም አቀፍ ማሪታይም ድርጅት እ.ኤ.አ. በ፪ሺ፩ ያወጣው ኮንቬንሽን በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

## ፫. የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ሥልጣን

የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ኮንቬንሽኑ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር ፲፱ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Convention

The Convention on Civil Liability for Bunker Oil Pollution Damage adopted in 2001, by the International Maritime Organization is hereby ratified.

## 3. Responsibility of the Ministry of Transport and Communications

The Ministry of Transport and Communications is hereby authorized to undertake, in cooperation with the concerned governmental organs, all acts necessary for the implementation of the Convention.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 27th day of January, 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**